# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የኢላላ ገዳ ማከፋፈያ ጣቢያ ድሮና ዘንድሮ

የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያዎች ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ያመረቱትን ኃይል ወደሚፈለገው ቦታ የማድረስ ተልዕኮን የሚወጡ ናቸው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የሀገራችን ኃይል የማመንጨት አቅም እያደገ መምጣቱን ተከትሎ ከከፍተኛ እስከ አነስተኛ ደረጃ ያሉ በርካታ የማከፋፈያ ጣቢያዎች እግር በእግር እንዲገነቡ ተደርጓል። በአንዳንድ ቦታዎች እንደአስፈላጊነቱ የአዳዲስ ማከፋፈያ ጣቢያዎች ግንባታ ሲከናወን በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ የነባሮቹን አቅም የማሳደግና የማስፋፋት ሥራ ተከናውኗል። የማስፋፊያ ሥራው ከወጪ፣ ከጊዜና ከግንባታ ቦታ አንጻር እንደ አዳዲሶቹ ከፍ ያለ በጀት የሚጠይቅ አለመሆኑ እንዲሁም በነባሮቹ ማከፋፈያ ጣቢያዎች የሚታየውን የቴክኖሎጂ ክፍተት ከመሙላት አንጻር ጥቅሙ ከፍ ያለ መሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ።



ኢንጅነር ክቡ ለማ

ኢንጅነር ክቡ ለማ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኢላላ ገዳ ማከፋፈያ ጣቢያ ኃላፊ ናቸው። እርሳቸው እንደሚያስረዱት፤ ጣቢያው በኦሮሚያ ክልል ቢሾፍቱ ከተማ ወጣብሎ በ1981 ዓ.ም የጋፋት አርማመንት ፋብሪካ መገንባትን ተከትሎ የተመሠረተ ነው። ጣቢያው ለአንድ ፋብሪካ ብቻ አገልግሎት እንዲሰጥ ታስቦ በደርግ ዘመነ መንግሥት የተገነባ ቢሆንም ከጊዜ በኋላ ግን ለሌሎች ፋብሪካዎችና ለአካባቢው ማኅበረሰብ አገልግሎት እየሠጠ የሚገኝ ነው። በአካባቢው የኃይል ፍላጎት እያደገ መምጣቱን ተከትሎ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ የማስፋፊያና አቅምን የማጠናከሪያ ሥራዎች ተሠርተውለታል።

ቀደም ሲል ጣቢያው በማኑዋል የሚሠራና የቴክኖሎጂ ክፍተቶች ያሉበት፤ በአንድ ትራክ ብቻ የሚሠራ ስለነበር ኃይል የመቀበል፣ የመሸከምና የማስተላለፍ አቅሙ ውስን ነበር። በዚህም የተነሳ ከፍተኛ መጨናነቅ ይታይበት ነበር ይላሉ ኢንጅነር ክቡ። በጣቢያው ላይ የሚስተዋለው የኃይል መጨናነቅ አደጋ ይፈጥራል የሚል ስጋት እንደነበረውም ጠቅሰዋል። ነባሩ ጣቢያ 12 ሜጋ ቮልት አቅም የነበረውና አራት ባለ 15 ሺህ ኪሎ ቮልት ወጪ መስመሮች ያሉት ነው። ምንም እንኳ ጣቢያው በዋናነት የጋፋት ፋብሪካ መሠረት አድርጎ የተመሠረተ ቢሆንም አንዱ ወጪ መስመር ቀጥታ ለጋፋት ፋብሪካ እየሠጠ ቀሪዎቹ ሦስት መስመሮች ደግሞ ለአካባቢው ማኅበረሰብና ለቢሾፍቱ ከተማ ጥቅም ይሠጡ ነበር።

በቢሾፍቱ ከተማ ፋብሪካዎች እየተስፋፉ በመምጣታቸውና ከተማውም እያደገ በመሄዱ በዚያው ልክ የኃይል ፍላጎት አድጓል የሚሉት ኢንጅነር ክቡ፤ በአካባቢው እያደገ የመጣውን የኃይል ጥያቄ ለመመለስ ጣቢያው የማስፋፊያና አቅምን የማሳደጊያ ሥራዎች ተሠርተውለታል። የማስፋፊያ ሥራውን የሠራው ሲኖ ሃይድሮ የተባለው የቻይና ኩባንያ ነው። በሥራው ሂደትም ሙያተኞች እያንዳንዱን የሥራ ሂደት የመመልከት ዕድል በማግኘታቸው የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲያደርጉ አስችሏቸዋል። ሠራተኞች ባገኙት ልምድና እውቀት መሠረት ከሲስተም ውጪ የሚሆን ኃይልን ወደ ሲስተሙ እንዲገባ የማድረግና ሌሎች ቀለል ያሉ ጥገና ሥራዎችን ማከናወን ችለዋል።

ጣቢያው አቅምን የማሳደጊያ ሥራዎች ከተሠሩለት በኋላ ከማኑዋል ወደ ዲጂታል አሠራሮች ተሸጋግሯል። ቀደም ሲል በነበረው አሠራር በተለይም ዘይታቸው በወቅቱ ካልተቀየረ ሊፈነዳና እሳት ሊፈጥር ስለሚችል በየሦስት ወሩ ፍተሻ እና የዘይት ቅየራ ይሠራ እንደነበር ያስታወሱት ኃላፊው፤ አሁን ባለው ቴክኖሎጂ ብሬከሮች ሲልድ ወይም ሽፍን መሆናቸውንና ዘይት የሚጠቀሙ አለመሆናቸውን ተናግረዋል። እንደአስፈላጊነቱ የተሞላላቸው ጋዝ ከጌጁ ከወረደ ወይም ካለቀ ብቻ ይሞላላቸዋል ብለዋል።

አዲሱ ማከፋፈያ 31 ነጥብ አምስት ሜጋ ቮልት ያለውና አራት ባለ33 ሺህ ኪሎ ቮልት ወጪ መስመሮች እንዲኖሩት ተደርጎ የተገነባ ነው።

በጣቢያው መስመሮች ላይ የነበረው መጨናነቅ ቀንሷል። አሁን በተደረገው ማሻሻያ የሚንጠባጠብ ኃይል እንዳይኖር ተደርጓል፤ አዲሱ ማከፋፈያም አራት ወጪ መስመሮች አንድ ባለ 33 ኪሎ ቮልት ለፋብሪካ የሚሰጥ ሲሆን፤ ሦስቱ ባለ 33 ኪሎ ቮልት ወደ ቢሾፍቱ ከተማ የሚሄዱ ናቸው። ባለ33ቱ ከተማ ከደረሰ በኋላ ወደ 15 ኪሎ ቮልት ተቀይሮ እንደአስፈላጊነቱ ለፋብሪካዎችና ለተለያዩ አገልግሎቶች ይውላል። በአዲሱ አሠራር የሚባክን ኃይል ሳይኖር የተጨነው ኃይል ሙሉ ለሙሉ ወደ ተፈለገው ቦታ ይደርሳል።

የማስፋፊያ ሥራው በሚሠራበት ጊዜ ለአካባቢው ሰዎች ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ፈጥሮ እንደነበር የተናገሩት የጣቢያው ኃላፊ፤ ጣቢያው ከከተማ ርቆ መገኘቱ በገጠራማ አካባቢ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎችንም የመብራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻሉ ሌላው ጥቅም እንደሆነ ጠቅሰዋል። የኤሌክትሪክ አቅርቦቱ ወደ ፊትም የአካባቢው ማኅበረሰብን አኗኗር ሊቀይርና ችግሮችን ሊያቀል ይችላል ይላሉ። ለምሳሌ ኅብረተሰቡን የንጹህ ውሃ ተጠቃሚ ማድረግ ሲታሰብ ውሃው ካለበት ቦታ ተስቦ ወደ ተፈለገበት ቦታ እንዲደርስ የኤሌክትሪክ ኃይል ያስፈልጋል ብለዋል። የማስፋፊያ ሥራው ከተሠራ በኋላ ባለሀብቶች የኤሌክትሪክ ኃይል ጥያቄ እያቀረቡ ናቸው። ከከተማው ፈጣን እድገትና ከፋብሪካዎች መስፋፋት አንጻር ወደፊትም የጣቢያውን አቅም የማሳደግና የማስፋፋት ሥራ ሊሠራ እንደሚችል ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል